**Kinijit North America Association of Support Organizations (KNAASO)**
766 Rock Creek Church Rd., NW. Washington DC, 20010
Telephone: (202) 541-0556. FAX: (202) 541-0557
www.kinijitna.org

መጋቢት 29 ቀን 1999 ዓ/ም

ይድረስ ለመላው የቅንጅት አመራር አባላት
ይድረስ ለነጻ ፕሬስ አባላትና የዴሞክራሲ ተሟጋቾች
ቃሊቲ ወህኒ ቤት

የተወደዳችሁ መሪዎቻችን ሆይ!

በውጭው ዓለም የምንገኝ ወገኖቻችሁ ቃሊቲ ከምትገኙት የህሊና እስረኞች የምንለይበት አንደኛው መንገድ ያሰብነውንና ያለምነውን በነፃ ለመወያየት፤ እንዲሁም በነፃ የፍርድ አደባባይ ለመቆም ባለን ዕድል ነው። ከዚያ በተረፈ ግን ባገራችን ጉዳይ የመጨነቁና የመጠበቡ፤ በህዝባችን ሰቆቃ እንቅልፍ የማጣቱ፤ የነገይቱ ኢትዮጵያ ሠላምና መረጋጋት የሰፈነባት፤ ፍቅርና አንድነት የገነነባት ሆና እንድትገኝ የመጣሩን የታሪክ ሃላፊነት በናንተው ፋና ወጊነት እንደተሰለፍንበት እንገኛለን።

የወያኔ ኢሕአዴግ ችሎት የፈጠራ ክሱን ወዲያና ወዲህ ሲያንከባልል ለብዙ ትዝብት ተጋልጧል። ዳኞቹ፤ የሃሰት ምስክሮቹ፤ አቃቤ ሕጉና የቀጠሮ ማራዘሚያ ሰበቦቹ ከአስቂኝ ደረጃ አልፈው ለብዙዎች የቁጣና የቁጭት ምንጭ ሆነዋል። ታዲያ ዛሬ ልንጽፍላችሁ የተነሳነው ይህንንኑ አስመልክተን ነው።

የዓለም ሕዝብ ዓይኑን ተክሎ በሚከታተለው የፍርደ-ገምድሎች ችሎት ውስጥ የፈጠራ ክሱ እርቃኑን ከቀረም በኋላ ለዴሞክራሲ፤ ለመብትና ለአንድነት የቆማችሁትን ውድ የኢትዮጵያ ልጆች በሃገር ክህደት  መፈረጁ የወያኔ ኢሕአዴግን አረመኔነት፤ የዳኞቹን ካድሬነት በድጋሚ የሚያረጋግጥ ነው። የችሎቱ የሁለት ዓመት ሂደትም ሆነ የሮቡ ለቱ ውሳኔ በመሰሪነቱ ተወዳዳሪ አይገኝለትም። አላማው፤ የናንተን ቅስም ለመስበር፤ የዲሞክራሲ ትግሉን እልህ ለመፈታተን፤ ደጋፊዎችን በተስፋና በጥርጣሬ ስሜቶች ውስጥ ለማንገላታት፤ የሚታለልለት የለም እንጂ በዓለም ሕዝብ ፊት የፍትሕ ሂደት እንዳለ ለማስመሰል፤ ሌሎችም ሊገኙበት ይችላሉ።

ውድ መሪዎቻችን!

ምክንያቶቹ ምንም ይሁኑ ምን ልንዘነጋቸው የማይገቡን ቁምነገሮች አሉ። መጀመሪያውኑ የተሠለፍንበት ዓላማ ፍትህንና ዲሞክራሲን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፈን ወይንም በዚህ ጥረት ውስጥ አስተዋጻኦ ለማድረግ ስለሆነ ይህ ፍፃሜ እስኪያገኝ ድረስ ቀበቶአችን እንደማይላላ ቃል ኪዳናችንን እናድስላችኋለን። ለፍትሕ መቆምና ለዴሞክራሲ ጠበቃ መሆን መብታችን ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ ግዴታችንም እንደሆነ እናውቃለን። የሰው ልጅ በደመ ነፍስ ከሚንቀሳቀሰው ምድረ አራዊት የሚለየው በዚህ የግንዛቤ ችሎታው ካልሆነ በስተቀር ሌላማ በምን ይለያል?

በአንጻሩ ደግሞ ለፍትህና ለመብት መቆም ከአምባገነኖች፤ ከጉልተኞችና ከራስ ወዳዶች ጋር በጽኑ መፋተግን፤ አንዳንዴም መዋደቅን እንደሚጠይቅ ከተገነዘብን ቆይተናል። የዲሞክራሲ ትግል እልህ አስጨራሺና አንዳንዴም ተስፋ አስቆራጭ የሚሆንበት ጊዜ አለና ከቶውንም ለነዚህ ወጥመዶች ተመቻችተን አንገኝላቸውም። ህማማት የጸሎትና የመስዎዕትነት መታሰቢያ ሳምንት ነውና በፀሎት የምናምን፤ "ጽናትን፤ ብልሃትን፤ አለመረበሺን፤ ነገሮችን ከስሜታዊነት ውጭ የማየትና የመተንተን ፀጋን አላብሰን" ብለን እንፀልያለን። እናንተም የሞቀና የደመቀ ቤታችሁን ትታችሁ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቤዛ ለመሆን የቆረጣችሁበትን ቀን በአንክሮ እንዘክራለን። ፈጣሪያችን በናንተ ፅጋ ስላደለንም እናመሰግነዋለን።

የኢትዮጵያን የፖለቲካ ታሪክና የዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታዎችን በውል ያገናዘበው ቅንጅት ለኢትዮጵያ ይበጃል ብሎ የመረጠው ስልት ሠላማዊ ትግልን ነው። አባላቱና ደጋፊዎቹም በዚህ ስልትና በሌሎች የፓርቲው ራዕዮቹ ስለተማረክን ነው ለቅንጅትና ለመርሆቹ መጠነ-ሰፊ ድጋፍና መስዋዕትነት እየከፈልን ያለነው። የናንተ የመንፈስ ጽናትና ትግሉ የሚጠይቀውን የመጨረሻ መስዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀት በዚህ ዘመን ላለነው ብቻ ሳይሆን ለመጭዎቹም ትውልዶች የሚተርፍ የሞራል የበላይነት አላብሶናልና መንጊዜም ባለውለታችሁ ነን።

እዚህ ላይ የሠላማዊ ትግል አባት የሆነው ምህተማ ጋንዲ ያስተማረውን ቁምነገር እንደገና እናስታውሳችሁ። ... "በመጀመሪያ ይንቁሃል፤ ከዚያም ይሳለቁብሃል፤ ከዚያም ይገድሉሃል፤ በመጨረሻ ግን ታሸንፋለህ" አለ። የወያኔ ይበልጥ እብሪተኛ፤ ይበልጥ ገዳይና ይበልጥ ይሉኝታቢስ መሆን የርሱን መጠናከር ሳይሆን የመውደቂያው ጊዜ መቃረቡን የሚያበስር እምቢልታ ነው። ወያኔ ልቡ ባበጠ ቁጥር እያሸነፍን ያለነው እኛ ነንና ትግላችንን ከምንጊዜም በበለጠ ስሜትና ስልት አጠናክረን እንቀጥላለን።

በነፍሰ ገዳዮች ኃይል ታጅቦና ለአንዳንድ መንግሥታት አጎብድዶ የሚገኝ የፖለቲካ እሴት ነገ ተኖ የሚጠፋ ጉም እንጅ ዘላቂና የተረጋጋ ሥርዎ መንግሥት ሊሆን የሚችል አይደለም። ከወያኔ ኢሕአዴግ ቡራ-ከረዩና ፍካሬ ጀርባ ብንመለከት የምናገኘው የተጨነቀና የተጠበበ መንግሥት እንደሆነ እናውቃለን። ከሕዝብ ጋር ፊትና ጀርባ የሆነ

መንግሥት፤ የዓለም ዓቀፍ መንግሥታትና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የሚኮንኑት ምንግሥት፤ የራሱም ሆነ ያጨፋሪዎቹ ጀንበር እያጨለመችበት ያለ መንግሥት በድቡሽት ላይ እንደተመሠረት ቤት ነው። አወዳደቁም ኃያል እንደሚሆን ኢሕአዴግ ሊገነዘበው ይገባል።

ውድ መሪዎቻችን!

ወደደም ጠላም ወያኔ ኢሕአዴግ ሠላምና መረጋጋትን በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲፈልግ የሚያስገድዱት ነባራዊ የሃገርና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች አሉ። በሕዝብና በመንግሥት መሃከል ያለው ቅራኔ መታረቅ ከማይችልበት ደርጃ የደረሰ መሆኑን ለመረዳት መለስ ዜናዊ መጠየቅ ያለባቸው ካድሬዎቻቸውንና ጀሮ ጠቢዎቻቸውን አይደለም። ከነርሱ የሚገኘው መረጃ ተአማኒነት ጉዳይማ በምርጫ 97 ወቅት ጉዱ ታይቷል። ላንዳፍታ እንኳ መነጽር ሰክተው፤ ባርኔጣ ደፍተው ወደህዝቡ ሰፈር ብቅ ቢሉ ውነተኛውን የወያኔ አኢሕአዴግ ጉድ ይሰሙ ነበር። ለነገሩማ ላገራቸው፤ ለሕዝባቸውና ለራሳቸው ደህንነት የሚጨነቁ መሪዎች እንዲህ ያደርጉ አልነበረም?

ውድ መሪዎቻችን!

ለኢትዮጵያ ሕዝብ የፈነጠቃችሁት የመብት፤ የነፃነት፤ የዕድገትና በኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት ጮራ በማንምና በምንም ሊጨልም ከማይችልበት ደርጃ ደርሷል። የዚህ ራእይ ተከታይና ሠራዊትም እያደገና እየተመነደገ ነው። የሰጣችሁንን የሠላማዊ ትግል አርማ አንግበን ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ እጅ ለጅ ተያይዘን አዲሲቷንና ታላቂቷን ኢትዮጵያ እንገነባለን። ይህ የማይታጠፍ ቃልኪዳናችን ነው፡፤

መልካም የትንሣኤ በዓል ለናንተና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንመኛለን!

በቅንጅት ሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ድርጅቶች ውስጥ የተሰባሰብን ወገኖቻችሁ።